# በእጅዎ ያለዉ ወንጌል

| | |
|---|---|
| የመዳን ቃል | ይሁዳ 3 |
| የዘላለም ሕይወት ቃል | ዮሃ 6 ÷ 68 |
| የተወደደ ቃል | መዝ ( 119 ) ÷ 97 |
| ለትምህርትና ለምክር የሚሆን ቃል | 1 ጢሞ 6 ÷ 3 |
| የሚፈለግና የሚደረግ ቃል | ዕዝ 7 ÷ 10 |
| የሚጠበቅ ቃል | 1 ጢሞ 6 ÷ 20 |
| | 1 ዮሃ 2 ÷ 5 |

መሆኑንስ ያዉቃሉ ?    ካወቁ ምን ያህል ጊዜ ይሰጡታል ? እርሱ ÷ በሰጡት ልክ ራሱን ይሰጥዎታልና ይበርቱ ፤ ያጥኑት ::

" ከወንጌል ጥቂትም " ጥቂት እየሞከረች  ያለችዉ ጥቂት እገዛ ካደረግሁ ብላ ነዉ እንጂ ÷ እርስዋ በፍፁም ፤ በፍፁም መፅሀፍ ቅዱስዎን አትተካምና እለት እለት መፅሀፍ ቅዱስዎን እንዲያጠኑ ታበረታታለች ::

# ምነዉ ?

የልቡ ምት ጨመረ ፤ ትንፋሽም አጠረዉ ፤ ሰነዘረ ! ሊጨርሰዉ ሊገላግለዉና እርሱም ሊገላገል :: ክፉ ጊዜ ÷ ክፉ ሰዐት ÷ ክፉ ትዕዛዝ ፤ ጨብጦ ባዶ ፤ ወልዶ መና ላለማሳደግ ፤ ላለማጎልመስ ፤ ላለመዳር ላለመኳል ፤ ክፉ ፤ እጅግ ክፉ ::

አዎ ! የልቡ ምት ጨመረ ፤ ትንፋሽም አጠረዉ ፤ የሰዉ ያለህ ! የገላጋይ የአስጥሉኝ ሲቃ ፤ ጩኸት ፤ ድምፅ በሌለበት :: ነደደ ዉስጡ ፤ ተቃጠለ አንጀቱ እንባ ሳግ ተናነቀዉ ኡ ! አለ  ዉስጡ ጮኸ ::

አብርሃም ! አብርሃም ! በብላቴናዉ ላይ እጅህን አትዘርጋ ! አንዳችም አታድርግበት :: የሚል ድምፅ ከላይ ከሰማይ መጣ :: አብርሃምም አይኑን አነሳ በኋላዉም እነሆ አንድ በግ በዱር ዉስጥ  ቀንዶቹ በእፀ ሳቤቅ ተይዞ አየ :: ( ዘፍ 22 ÷ 11-13 )

መተኪያ ÷ ለአብርሃም ልጅ ለይስሃቅ የሚሆን አንድ በግ ተገኘ ፤ ለልቡ ሀዘን ፤ ለዕንባ ለሳጉ ፤ ለጩኸቱ ለሰቀቃዉ :: ጩኸቱ ተሰማለት ፤ ተደመጠለት መተኪያ ተገኘለት ይስሃቅ

( ሉቃ 22 ÷ 42 ) " አባት ሆይ ÷ ብትፈቅድ ይህችን ፅዋ ከእኔ ዉሰድ " ብሎ ቢጣራ ፤ ቢጮህ በእንባ ምነዉ ሰሚ ጠፋ ፤ አድማጭ :: ምነዉ ? አባት በልጁ ጨከነ ፤ እንባ ÷ የደም ላቡን  እያየ ዝም ፤ ፀጥ አለ ::

የይስሃቅ ፅዋ ሲወሰድ ምነዉ ? የየሱስን የሚወስድ ጠፋ ? ምነዉ ሀገር ዝም ፤ ፀጥ አለ :: ምነዉ ምድር ጨለመች ፤ አላየሁም አልሰማሁም ፤ አለች ::

" በእዉነት ደዌአችንን ተቀበለ ÷ ሕመማችንንም ተሸክሞአል ፤
ስለ መተላለፋችን ቆሰለ ÷ ስለ በደላችንም ደቀቀ ፤
የደሕንነታችንም  ተግሳፅ በእርሱ ላይ ነበር ::
በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን !! "

ኢሳ 53 ÷ 4-5

" እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ፅድቅ እንሆን ዘንድ ኋጢያት ያላወቀዉን እርሱን ስለ እኛ ኋጢያት አደረገዉ "

2 ቆሮ 5 ÷ 21

እሰይ የኔ መተኪያ ÷ እሰይ የደሕንነቴ ጌታ ! እሰይ !

ይህ ኢየሱስ የእርስዎስ ነዉን ?

# የታጠበ መረብ

የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 5÷1-8

ጌንሳሬጥ ባሕር ዳር መጣ ፤ አላማዉን ሊፈፅም ፤ ወንጌልን ለማብሰር :: ሌላ ጉዳይ የለዉም ከወንጌል የተለየ ፤ ህይወት የሚሰጠዉን ዘለአለማዊ የሚያደርገዉን ፤ ከሞት ወደ ሕይወት የሚያሻግረዉን ወንጌልን ያስተምራል ፤ ይሰብካል ::

በባሕር ዳር ፤ በነፋሻዉ ስፍራ ÷ በማለዳ ደረሰ :: ምድር በፀሐይ ብርሐን ስትዋብ ፤ የሰዉ ተስፋ ለምልሞ ፤ ትላንትናዉን እረስቶ አዲስ  ቀን በአዲስ ሲጀምር  ጌታ ወንጌል ይዞ መጣ ::

በሙያዉ የተካኑት ለዘመናት ፤ ዛሬ ያልሆነላቸዉ ያልሰመረላቸዉ ፤ ድካም የተጫናቸዉ እነ ጴጥሮስ መረብ ሲያጥቡ የዉስጣቸዉ ተስፋ ተሟጦ ፤ ፊታቸዉ ቅጭም ብሎ :: አዝነዉ ተክዘዉ ::

መረብ አጠባ :- ለምን  መረብ አጠባ ? ለሊቱን ሙሉ ካላጠመዱ ፤ አንድም አሳ ካልያዙ ፡ ለምን መረብ አጠባ ? ደርሶ ድካም እንደገና ፤ መረብ አጠባ ::

መረብ ከባሕር ከወጣ በኋላ ፤ አገልግሎቱን ከጨረሰ በኋላ ካልታጠበና ተዘርግቶ ካልተወጠረ  እርስ በርሱ ይያያዝና ለነገ የማይጠቅም እቃ ይሆናል :: ጴጥሮስ ያንን ያዉቃል ፤ ለዘመናት አድርጎታል ለዚህ ይሆን መረብ አጠባ ?

ምነዉ ተስፋ አልቆረጠ ? ቀሎት ነዉ ለሊቱን ሙሉ መድከሙ? ማለዳ መረብ ማጠቡ ? ምን ሰርቶበት ያጥበዋል ? ቢተወዉ ÷ እርግፍ አድርጎ ፤ ቢያርፍ ቢገላገል ምን አለ ?

ጌንሳሬጥ ሲመጣ ጌታ :- ታጥቦ ለሚቀጥለዉ አገልግሎት ያልተዘጋጀዉን መረብ ወደ ባህር ይጣል ዘንድ ያዝ ይሆን ? ምን ይመስሎታል ?

አሳ የለም ዛሬ ፤ ለሊቱን ሁሉ ደከምን ፤ ለምንል ÷ ጴጥሮስ ከኔ ተማሩ ይለናል :: መረቤን ወደዚያ ወርዉሬ ለመሄድ እኔም ትንሽ ነበር የቀረኝ ÷         ግ-ን-    ነገ ፤ ግድ የለም ፤ ነገ ብዬ መረቤን ለነገ ሳዘጋጅ ዛሬ ኢየሱስ መጣ ነዉ የሚለን ፤ አወን ዛሬ ----መረቤም ሞላ ::

ለምን ተስፋ ይቆርጣሉ ? ይልቅ መረብዎ የታጠበ የተዘጋጀም ይሁንልዎ ::

ባልተዘጋጀ አይሰራምና ::

# ወዳጅ

“አንተ ሰይፍና ጦር ጭሬም ይዘህ ትመጣብኛለህ ÷ እኔ ግን ዛሬ በተገዳደርከዉ በእግዚአብሔር ስም እመጣብሀለሁ ”    1ሳሙ 17÷45

ብሎ ጎልያድን ያህል ጀግና በጠጠር ዘረረዉ ፤ ወደቀ ÷ ህዝብ ጉድ አለ ፤ አልጠበቁም ይህ ይሆናል ብለዉ ፤ ፍርሀት ጭንቀት በነገሰበት በዛ በሳኦል ጦር መካከል ድንገት ተገኝቶ ታደጋቸዉ ባምላኩ ታምኖ ነፃ አወጣቸዉ ::

ምድር ተደንቋልና ፤ ከምርኮ በኋላ ዳዊትን ወሰዱት ሳኦል ፊት አቀረቡት ፤ አወን ከዛን ጊዜ ጀምሮ 1ሳሙ 18÷1 “ የዮናታን ነፍስ በዳዊት ነፍስ ታሰረች ዮናታንም እንደ ነፍሱ ወደደዉ ”

ለምን ? ለምን ዮናታን ዳዊትን እንደነፍሱ ወደደዉ ? በጀግንነቱ ነዉን ? ምን ይላሉ እርስዎ ?

ፍልስጥኤማዉያን የእስራኤልን ልጆች የሚያስጨንቁት አያሌ ጊዜ ነዉና ከዚህ በፊትም እስራኤልን አስጨነቁ ÷ ሕዝቡ ሸሸ  ተሸሸገ ÷ ሮጠ ከጦሩ ሜዳ አመለጠ ፤ ሳኦል ፈራ ምድር ተንቀጠቀጠች  በዚህ ጊዜ አንድ ጎበዝ አንድ ጀግና ና ! አለ      1ሳሙ 14÷6
“ በብዙ ወይም በጥቂቱ ማዳን እግዚአብሔርን አያስቸግረዉምና ፤ ና ! ”
ብሎ በአምላኩ ታምኖ ድልን ለእስራኤል ልጆች ያስገኘዉ ይሄ ዮናታን ነበር ::

ዮናታን ዳዊትን ወደደዉ :: ለምን ? እርሱ በሚታመንበት እግዚአብሔር የሚታመን ፤ ጉልበቱና ደገፋዉ የሚያደርግ አንድ ሰዉ ድንገት ተገኝቷልና ዮናታን ወደደዉ ÷ አፈቀረዉ ፤ ነፍሱም በዳዊት ነፍስ ታሰረች ::

ተወዳጁ ፤ ተፋቀሩ ፤ ተያያዙ ፤ አንድ ሆኑ ::    ወዳጅ :-1ሳሙ 23÷16 ዳዊት በንጉስ ሳኦል እጅ እንዳይሞት በሸሸና በጥሻ ዉስጥ በተሸሸገ ጊዜ ዮናታን “ ወዳጅ ” መጣና በእግዚአብሔር ላይ ባለዉ እምነቱ እንዲበረታ አበረታታዉ ::

ዮናታንና ዳዊትን ያወዳጃቸዉ በአምላካቸዉ ላይ ያላቸዉ ፅኑ እምነት ነዉ እንጂ ሌላ እንዳልሆነ ግልፅ ነዉ ::

እርስዎስ ከወዳጆ በምን ተወዳጁ ????

የእርስዎ ጓደኛ ከአምላክዎ ጋር እንዴት ነዉ ????

እርስዎስ?????

# <u>ሮቤል !</u>

ልክ ነዉ ! የመጀመሪያ ልጅ በመሆኑ ብቻ ፤ ኀላፊነት ግዴታም አለበትና ( ዘፍጥ 30÷14 ) ወጣ ሄደ ፤ በኀዘን ለቆዘመችዉ ፤ ወዳ ላልተወደደችዉ ፤ አፍቅራ ላልተፈቀረችዉ ለእናቱ ለልያ እንኮይ ይዞላት በመምጣት የተሰበረ ልብዋን ፈወሰዉ ፥ አከመዉ የበኩር ልጅነቱን ግዴታ ተወጣ ፡፡

የያዕቆብና የልያ የመጀመሪያ ልጅ ( በኩር ) ፤ የደስታቸዉ መጀመሪያ ፤ የቤታቸዉ ማሞቅያ ሮቤል ፦ (እግዚአብሔር መከራዬን አይቶአልና ) ስትል እናቱ የሰየመችዉ ሮቤል ፦ ወንድ መመኪያ ፤ መታመኛ የቤቱ ፤ የሀብቱ ወራሽ ፤ የስማቸዉ መጠሪያ ፤ ምሳሌ ፤ ክብር ፤ጌጣቸዉ ሮቤል ፡፡

ሮቤል ! የያዕቆብን ቤትና ልብ አሞቀዉ ፤ አሳመረዉ ፡፡ ደስታንም ለቤቱ ጨመረ ፡፡ ወንድሞች ተወለዱለት ፤ በዙለት በታላቅነቱ ከበረ ፤ ደስ ተሰኘ ፡፡ እርሱ ነዉና መሪያቸዉ ፤ ምሳሌአቸዉ አለቃቸዉ ባለመብት ወራሽ ፡፡

አስሩ ወንድሞቹ በዮሴፍ ላይ መክረዉ ሊገድሉት በቆረጡ ጊዜ ( ዘፍ 37 ÷ 22 ) ደም አታፍስሱ በማለት እንዳይገድሉት መከራቸዉ ለአባቱ ሊመልሰዉ ወዶአልና ፡፡ ዋዉ ! ታላቅ ፤ ዋዉ ! ሮቤል  ትልቁ የቤቱ ለወንድሙ መሟገቱ ፡፡  እሰየዉ ! ነዉ ፡፡

አባትየዉ ያዕቆብም የመሞቻዉ ሰዐት በደረሰ ጊዜ ፦ በረከቱን ሊሰጣቸዉ ፤ ሊያወርሳቸዉ ሰብስቦ ( ዘፍ 49 ÷ 3 )

ሮቤል ፦

አንተ በኩር ልጄና ኀይሌ
የጉብዝናዬ መጀመሪያ ነህ
የክብር አለቃ ፤ የኀይል አለቃ

በማለት በእርግጥም ክብሩንና አለቅነቱን በወንድሞቹ መካከል ሲገልፅ ማንኛዉም አባት ለበኩር ልጁ መስጠት የሚገባዉን ክብርና ሙገሳ ባለመንፈግ ሲሆን ( ዘፍ 49 ÷ 4 ) ስንደርስ

ሮቤል ፦

እንደ ዉሀ የምትዋልል ነህ
አለቅነት ለአንተ አይሁን
ምክንያቱም ፦ ወደ አባትህ መኝታ ወጥተሀልና
አረከስኀዉ ወደ አልጋዬም ወጣ

በማለት ( ዘፍ 35 ÷ 22 ) ያደረገዉን የዝሙት ሀጢያት በማስታወስ ብኩርናዉን ከለከለዉ ፤ ነፈገዉ ፤ ወሰደበት ፤ አሳፈረዉ አዋረደዉ ሮቤል ፦ ዝሙት ዋጋ አስከፈለዉ ፤ ታላቅ ክብሩን አሳጣዉ ፤ ዋ ! ዉ

“ ከሴት ጋር የሚያመነዝር አእምሮ የጎደለዉ ነዉ
እንዲሁም የሚያደርግ ነፍሱን ያጠፋል፡፡ ቁስልንና ዉርደትን
ያገኛል፥ ስድቡም አይደመሰስም ፡፡ ”  ምሳሌ 6 ÷ 32 – 33
ለዚህ ይሆን ?

# <u>የደም እጅ</u>

ንጉስ ሳኦል ባለመታዘዙ ምክንያት መንግስቱ እንደሚወሰድበት ሲነገረዉ እግዚአብሔር እንደ ልቡ የሚሆን ሰዉም እንዳዘጋጀ በመግለፅ ያም ሰዉ ዳዊት እንደነበረ ( 1ሳሙ 13 ÷14 ) ተፅፎልናል ፡፡

ለእግዚአብሔር እንደ ልቡ የሚሆን ሰዉ ፥ የሚቀናበት ሰዉ ነዉ ፡፡ 1ሳሙ 24 እና 26 ዳዊት ሳኦልን በአመቺ ስፍራ ፤ ሊገድለዉ በሚችልበት ስፍራ አገኘዉ ነገር ግን ሳይገድለዉ የቀረዉ “ እግዚአብሔር የቀባዉ ላይ እጄን አላነሳም በማለት ነበር ”

ዳዊት ከበግ እረኝነት እግዚአብሔር ራሱ አንስቶ ንጉስ ያደረገዉ ሰዉ ፥ አንበሳና ድብ በጎቹን ለመንጠቅ ይመጣ ነበር እኔም በአምላኬ ስም አስጥለዉ ነበር ፡፡ አንተ ጭሬና ጎመድ ይዘህብኝ ብትመጣ እኔ አንተ ዛሬ በተገዳደርኀዉ በአምላኬ በእግዚአብሔር ስም እመጣብኀለሁ ብሎ ጎልያድን ያህል ጀግና የዘረረዉ በአምላኩ ስም ታምኖ ነበርና እዉነትም እንደ እግዚአብሔር ልብ የሚሆን ሰዉ ያሰኘዋል ፡፡

እስራኤልን አንድ ለማድረግ ባደረገዉ ፍልሚያ ሁሉ አምላኩ እግዚአብሔርን  ቀድሞ እየጠየቀና እያስከተለ ድልን በመቀዳጀት አንድነትን ያመጣ ዳዊት ፥ እልፍ ገደለ የተባለ ዳዊት ፥ የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ እየሩሳሌም በክብር ያመጣ ዳዊት ፤ የእግዚአብሔር ቤት ስራ ላይ ግን ( 2ሳሙ 7÷1-17 ) ተከለከለ ፡፡

እንደ እግዚአብሔር ያለ ልብ ያለዉ ሰዉ እንዴት ይከለከላል ? በዉኑ እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር አይደለምን ?

እጀ <u>ደማም</u> ሰዉ በእግዚአብሔር ቤት ዉስጥ ስራ እንዳይሳተፍ ለምን ተከለከለ ? ደም አፍሳሽ በእግዚአብሔር ቤት አገልግሎት ዉስጥ እንዳይሳተፍ ለትምህርት ተፅፎልን ይሆን ?

ምን ያህል በእግዚአብሔር የተወደዱ ቢሆኑ ፥ ምንም ያህል እግዚአብሔርን በመታመን የሚኖሩ ቢሆኑ የቤቱን ስራ በተመለከተ ግን እግዚአብሔር እንዲህ ይላል እኔ ላንተ ቤት እሰራልኋለሁ እንጂ አንተ ለኔ ቤት ስራ አትሆንም እጀ <u>ደማም</u> ነህና ፡፡

ስለዚህ ተዉ ወንድምህን አትግደለዉ !!!!!!!!

እጅህን ከደም ከልክለዉ ፡፡

# አይመስልዎትም ?

ቲቶ ምዕራፍ 2 ፥ 11-13

" ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ፀጋ ተገልያአል ። ይህም ፀጋ ኋጢያተኝነትንና አለማዊን ምኞት ክደን የተባረከዉን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድሀኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለፅ እየጠበቅን ራሰችንን በመግዛትና በፅድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል ።"

ስለዚህ ፀጋ እግዚአብሔር ሊመሰገን ይገባዋል ። ሰዎችን ሁሉ ለማዳን የተገለፀ ፀጋ ነዉና ። ለ-ደ-ህ-ን-ነ-ት

1. ይህ ፀጋ ነዉ ኀጢያተኝነትንና አለማዊ ምኞትን እንድንክድ የሚያደርገን ።

2. ይህ ፀጋ ነዉ የኢየሱስን መገለፅ እየጠበቅን እንድንኖር የሚያስተምረን ።

3. ይህ ፀጋ ነዉ ራሳችንን እንድንገዛ የሚያስተምረን ።

4. በፅድቅ እንድንኖርም የሚያስተምረን ይሄዉ ፀጋ ነዉ ።

5. እግዚአብሔርንም በመምሰል እንድንኖር የሚያስተምረን ሌላ ሳይሆን ይሄዉ የእግዚአብሔር ፀጋ ነዉ ።

ለዚህ ነዉ ፡-"ፀጋዉ በእምነት አድኖአችኋልና ፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነዉ እንጂ ከእናንተ አይደለም ፤ ማንም እንዳይመካ ከስራ አይደለም ።" ኤፌ 2 ፥ 8

ይህን የመሰለ የእግዚአብሔር ፀጋ ላይ ምንም አለመጨማመር ነዉ ።

ዝም ፤ ፀጥ ፤ እረጭ ብሎ በፊቱ መቀመጥ !

አ---ይ---መ---ስ---ል---ዎ--ት--ም ??

## በወደድሁ ነበር

( ዘፍ 17 ፥ 18 )

ከሳራ ሳይሆን ከአጋር በተስፋ ቃል ሳይሆን በስጋ የተወለደ "እስማኤል በፊትህ ቢኖር በወደድሁ ነበር " ።

ለአብርሀምና ለሳራ እግዚአብሔር ልጅን እሰጣለሁ ባለዉ መሰረት ( ዘፍ 15 ) ሲጠብቁ ፤ ጥበቃዉ ስላሰለቻቸዉ በምክክርና በስምምነት ወደዉ ከእግዚአብሔር ሀሳብ ዉጭ በመሄድ አብርሀም ከሰራተኛዉ ከአጋር እስማኤልን ወለደ ።

አብርሀም ይህንን ከአምላካቸዉ ሀሳብና እቅድ ዉጭ የተወለደዉን እስማኤልን ከአስራ አምስት አመት በላይ በማሳደግ ማጎልመሱ ሳያንስ ዛሬ እግዚአብሔር አምላካቸዉ እንደ ተስፋ ቃሉ ልጅን ሊሰጣቸዉ ሲመጣ አብርሀም " እስማኤል በፊትህ ቢኖር በወደድሁ ነበር " አለዉ ።

እባክህን እግዚአብሔር ሆይ ! ይህንን እስከዛሬ ያሳደኩትን ሀጢያቴን ባርክልኝ ፤ አሳድጌዋለሁና ወድጄዋለሁና ያንተ ይቅርብኝ ይህን በስጋዬ ፈቃድ ያመጣሁትን ልጄን ባርክልኝ ፤ ይስህቅ ይቅርብኝ ።

የዛሬ አብርሀሞች ፥ ሀጢያትን የምናሳድግ ።

የዛሬ አብርሀሞች ፥ ሀጢያትን በንስሀ ሳይሆን ፤ ለባርክልኝ ወደ ጌታ የምናመጣ ።

የዛሬ አብርሀሞች ፤ ጥበቃ የሰለቸን ፤ ሌላ መንገድ የምንሻ

አብርሀም አንዳች ያስተምረን ይሆን ?

## መፅሀፍ ቅዱስ

ሁሉ ሀጢያትን ሰርተዋል
ሮሜ 3 ፥23

የሀጢያት ደሞዝ ሞት ነዉ
ሮሜ 6፥23

የሀጢያትን ሞት ክፍያ
ኢየሱስ ወሰደ ሮሜ 8 ፥ 1-2

ሀጢያት እያወቅን አ ናድርግ
ያዕ 4 ፥ 17

ጌታ ይቅር ሊለን የታመነ ነዉ
1 ዮሀ 1 ፥ 8-9

ይለናል !

## ይሄዉ መፅሀፍ

የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታዉቁምን ?

1ቆሮ 3 ፥ 16

ወይስ ስጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረዉ የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደሰ እንደሆነ አታዉቁምን ?

1ቆሮ 6 ፥ 19

የጠራችሁ ቅዱስ እንደ ሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ ።

1ጴጥ 1 ፥ 16

ይለናል !

## “ ነገ ”

ዘፀ 8 ÷ 10

ሕዝቤን ልቀቅ ! አገልጋዬ ነዉና :: ለእኔ የተለየ ነዉና ሕዝቤን ልቀቅ ! ሳወርሰዉ ያለኝ ምድር አለና ፤ ሕዝቤን ልቀቅ ::ፈርኦን ይህንን አምላካዊ ትዕዛዝ እንቢ በማለቱ በእርሱና በሕዝቡ ላይ ታላቅ መቅሰት ወረደባቸዉ ፤ ተጨነቁ ፤ ተሰቃዩ ፤ እሪታ ሆነ ::

በምድረ ግብፅ ያለዉ ዉሀ ሁሉ ደም ከመሆኑ የተነሳ ግብፃዉያን የሚጠጡት ዉሀ ሳይኖር ሰባት ቀን አለፈ ::
( ዘፀ 7÷25 ) ፈረኦን እንቢ ፤ ሕዝቡን አለቅም አለ :: በምድረ ግብፅ ጓጉንቸር ( እንቁራሪት ) ዘነበ :: በቤት ፤ በዉጭ ጓጉንቸር በምግባቸዉና በመጠጣቸዉ ጓጉንቸር ::

ግብፃዉያን እጅግ ተጨንቀዋልና ጩኸት ብቻ ሆነ ለቅሶና እንባ ግብፅን ሸፈነ :: ፈርኦን ሙሴንና አሮንን አስጠርቶ ( ዘፀ 8÷8 ) ጓጉንቸሮቹ ከእኔ ከሕዝቤም እንዲያርቅ ወደ እግዚአብሔር ፀልዩልኝ ፤ ለእግዚአብሔር ይሰዋ ዘንድ ሕዝቡን እለቅቃለሁ አላቸዉ ::

ፀልዩልኝ ፤ ጓጉንቸሩን ያመጣዉ ጌታ : ሊያስወግደዉም ይቻለዋልና ፤ እርሱ ብቻዉን ሀያል ነዉና ፀልዩልኝ ፤ ማልዱልኝ
ፀልይልኝ ÷ የሙሴ መልስ በጥያቄ ነበር :: ጓጉንቸሮቹ ከምድርህ እንዲወገዱ መቼ ልፀልይልህ ?

ፈርኦን ፦ እነዚህ ጓጉንቸሮች እኔንና ሕዝቤን አስጨንቀዋልና ከእነርሱ ጋር አንዲት ደቂቃ በተጨማሪ መሆን ስለማልፈልግ “ አሁን” ፀልይልን ከማለት ይልቅ “ ነገ ” ፀልይልን ማለቱ ፤ አንድ ተጨማሪ ቀን ከጓጉንቸሮቼ ጋር ልደር ማለቱ የሚያስደንቅ ቢሆንም ፤ ትምህርቱ ለእኛዉ ነዉ ::

መንፈሳዊ ሕይወታችንን ፤ ዕድገታችንን ፤ ትዳራችንን ቤታችንን ፤ አገልግሎታችንንም እየበላ ያለዉን “ ጓጉንቸር ” መሰል ነገር እያወቅን ፤ ወደንና ፈቅደን አቅፈን በመያዝ “ ነገ ” ነገም ሲመጣ ሌላ “ ነገ ” ለምንል “ ዛሬ ” ፀልየን በንስሀ እናስወግደዉ ዘንድ ለምክር ተፃፈልን :: “ ዛሬ ” አወን “ ዛሬ”

## የተከፈተ በር

ዉብ ነዉ ÷ ያማረ ቢሆንልን ፤ በየለቱ ቢሳካልን ፤ ነገር ቢሰምርልን ፤ በር ቢከፈትልን :: የተከፈተ በርን እግዚአብሔር ቢያደርግልን የማንወድ የለንም የተከፈተ በር ÷በትዳራችን ፤ በስራችን ፤ በትምህርታችን ፤ በየለት ገጠመኞቻችን የተከፈተ በር ፤ በር ፤ በር ----

ወዲህና ወዲያም ተመለከተ ÷ ማንንም አላየም ÷ ግብፃዊዉንም ገደለ ( ዘፀ 2 ÷ 12 ) የተከፈተ በር ማንም ተመልካች ፤ እማኝ የሌለበት ክፍት በር ጠላትን ለመበቀል ወገንን ለማስደሰት አመቺ ጊዜና ሰዐት ::

የተከፈተ በር ሙሴን 40 አመት በምድረ በዳ አንከራተተዉ :: በር ! ያዉም የተከፈተ በር ÷ አመቺ ሰዐት ፤ ግሩም ወቅት :: ነገር ግን እግዚአብሔር የሌለበት በር ፤ ክፍት በር ፤ መልካም ሽጋ የሚመስል በር የተከፈተ በር ::

ዉበትን ተላብሳለች ÷ በእርግጥም ዉብ ነች ያማረች ፤ የተዋበች ዞር ፤ ዞር ፤ ሰዉ የለም ታዛቢ ዋዉ ! የተከፈተ በር ፤ ጠየቀና ማንነትዋን አስመጣት በስዉር ፤ ማንም በሌለበት ወሰዳት ፤ የራሱ አደረጋት :: ( 2 ሳሙ 11 ÷ 1- ) ዳዊት በዘመኑ መከራን አየባት :: የተከፈተ በር ጌታ የሌለበት ::

ከምድር ሊያስወግደዉ በሚችልበት ሁኔታ ተገናኘዉ ፤ ወዳጆቹም “ እነሆ እግዚአብሔር ጠላትህን በእጅህ አሳልፌ እሰጠዋለሁ ÷ በአይንህም ደስ የሚያሰኝህን ታደርግበታለህ ብሎ የነገረህ ቀን እነሆ ዛሬ ነዉ ” ( 1 ሳሙ 24 ÷ 4 ) የወደድከዉን አድርግበት ( ግደለዉ ) አሉት :: እዉነትም የተከፈተ በር ፤ ወለል ያለ ፤ አመቺ ሰዐት ለመግደል ለመበቀል::

ዳዊት ግን ፦ በሩ የተከፈተ ነዉ ፤ ሁኔታዉ የተመቸም ነዉ ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር የለበትምና አላደርገዉም ፤ አልሞክረዉም አለ :: ጠላቴን በአመቺ ስፍራ አግኝቼዋለሁ ልገድለዉ አቅምም ነበረኝ ÷ ግን በዚያ ስፍራ እግዚአብሔርን አላየሁትምና አላደርገዉም ፤ አልሞክረዉምም ::

በተከፈተ በርዎ በእርግጥ እግዚአብሔር አለበትን ? ብዙዎቻችን የተከፈተ በር በር ስናይ የአምላካችንን በበሩ አለመገኘት ሳናስተዉል ችግር ዉስጥ እንገባ ይሆንን ?

አያሌ ያማሩና የተዋቡ ክፍት በሮች ÷ ባዶ በሮች ለማጥመድ ሆነ ብለዉ የተከፈቱ ዉብ በሮች አሉና ጠንቀቅ ነዉ !

አ-ይ-መ-ስ-ሎ-ት-ም

# እነዚህ እነማን ናቸዉ ?

ዘፍ 48 ÷ 8

ከላይ እስከታች ገልመጥ ሳያደርጋቸዉ እንዳልቀረ እርግጥ ነዉ ። በገፅታ ፤ በአቋማቸዉ ። በአለባበስ ፤ በእይታቸዉ ሌላ ፤ ፍፁም ሌላ ናቸዉና ግር ተሰኘ ። እንደለመደዉ ፤ እንዳደገበት የወጣቶች ገፅታ ፤ እይታ የላቸዉምና " እነዚህ እነማን ናቸዉ ? " አለ ያዕቆብ ።

" እነዚህ እነማን ናቸዉ ?" ግር የሚያሰኙ ፤ እኛን የማይመስሉ ከኛ ለየት ያሉ ። የእኛም የየለት ጥያቄ ነዉ ። ለየት ያለ ስናይ ፤ ካደግንበትና ከተለማመድነዉ ዉጭ ሌሎች ሲያደርጉ ስናስተዉል ፤ እንጠይቃለን " እነዚህ እነማን ናቸዉ " እንላለን ።

ያዕቆብ ፡- ዮሴፍን ከወንድሞቹ ይልቅ ይዉደደዉ እንጂ ከእርሱ የተወለዱትን ኤፍሬምንና ምናሴን ሊለያቸዉ አልቻለም ። ኤፍሬምና ምናሴ ከአባታቸዉ ከዮሴፍና ከግብፃዊት ሴት በግብፅ ነዉ የተወለዱት ስለዚህም ግማሽ ዕብራዊ ግማሽ ግብፃዊ ናቸዉና ግር አሰኙት ።
( ዘፍ 41 ÷ 45 )

አለባበሳቸዉ እብራዊም አይደለም እ--እ--እ --ግብፃዊም አይደለም መልካቸዉም አቋማቸዉም እንዲሁ ነዉ ። እነዚህ እነማን ናቸዉ?

ያዕቆብ በዘመኑ ካከናወናቸዉ መልካም ነገሮች ዋንኛዉ እነዚህን ልጆች እንደራሱ ልጆች መቀበሉ ነበር ። እ-ር-ስ-ዎ-ሳ ?

እርስዎና የእርስዎ ቤተ ክርስቲያን እንዴት ናችሁ ? ለየት ያሉትንም በፀጋቸዉ ያቅፋል ? ወይስ------------?

ያዕቆብ ምን ለየት ቢሉ ግማሽ ዕብራዊ ግማሽ ግብፃዊ ቢሆኑ ወ ሰዳቸዉ ተቀበላቸዉና ልጆቹ አደረጋቸዉ ። ዉብ ዉሳኔ !

መሳፍንት 4 ÷ 4 ጀምሮ የምናያት ዲቦራ የተባለች ፅኑ ሴት የማን ዘር ትመስልዎታለች ?የኤፍሬም እኮ ነች ።

ጌድዮንስ የማን ዘር መሰለዎ የምናሴ እኮ ነዉ ፤ አይገርምም " እነዚህ እነማናቸዉ ? " ግማሽ ዕብራዊ ግማሽ ግብፃዊ ናቸዉ ።

የሀና ልጅ ሳሙኤል ኤፍሬማዊ እንደሆነስ ያዉቃሉ ? እርሱም ግማሽ ዕብራዊ ግማሽ ግብፃዊ ነዉኮ ? ምን ይላሉ እርስዎ ?

እነዚህ እነማናቸዉ ? ብለዉ አይግፉአቸዉ ፤ ይቀበሉዋቸዉና የፀጋቸዉ ተጠቃሚ ይሁኑ ። በግድ እኛን መምሰል ፤ እንደኛ መልበስና መናገር የለባቸዉም ብዙ ሊያገለግሉና ብዙ ሊሮጡ የሚችሉ በቤተ ክርስቲያኖ ተቀምጠዉ እንዳያረጁብዎ ጥንቃቄ ሊያደርጉ ያስፈልጋል እግዚአብሔር ይርዳዎ !

አ-ይ-መ-ስ-ሎ-ት-ም ?

# ባለረኛዉ ራብተኛ

" ኢየሱስም ፡- ወጥቶ ብዙ ሕዝብ አየና እረኛ እንደሌላቸዉ በጎች ስለ ነበሩ አዘነላቸዉ ÷ ብዙም ነገር ያስተምራቸዉ ጀመር ። "

ማር 6 ÷ 34

ሕዝብ ! ቃል ተርቧል ፤ " <u>የእግዚአብሔር ቃል</u> " ለመማር ለመመከር ፤ ለመገሰፅና ለመፈወስ ። ሆ ! ብሎ ÷ ቤቱን ፤ መንደሩን ለቆ ሄደ ፤ ወጣ ፤ ገሰገሰ ፤ ማንም ሳያቆመዉ ተመመ ።

ራብ ነዉና ጨከነ ፤ ጥማት ነዉና ቆረጠ ፤ ሄደ ! ሄደ ! ኢየሱስን ከበበ ። በዉሃ ምንጩ ሰፈረ ÷ ሊረካ ከጥማቱ ፤ ሊጠግብ ከረሃቡ ወደደ ።

ምነዉ ሕዝብ ተራብ ? ምነዉ አካል ተጎዳ ? ምነዉ " እረኛ " እያለ ምነዉ ? ወገን ከሳ-ሳ ? ምነዉ ? ኧረ ምነዉ ?

ኧረ ! ሕዝብ ተመመ ፤ ሄደ ፤ ወጣ ፤ ነጎደ ÷ ዝም አትበል " እረኛ "

" ደካማዉ ምነዉ አልፀና ? ታማሚዉ አልተፈወሰ ? ሰባራዉ አልተጠገነ ÷ ባዛኙ አልተመለሰ ? የጠፋዉ አልተፈለገ ? ምነዉ ? ምነዉ ?

ሕዝ 34 ÷ 4

ምነዉ ! ንቃ ! ንቃ እንጂ እረኛ ! ሕዝብ እንዳይሆን " ባለረኛዉ ራብተኛ "

# አሎንባኩት በቤቴል

ገና በእናቱ ማህፀን ዉስጥ እያለ “ ገዢ ” እንደሚሆን በሰዉ

ሳይሆን በእግዚአብሔር የተመሰከረለት ያዕቆብ ( ዘፍ 25 ÷ 23 )

በሰዉ ሳይሆን በእግዚአብሔር “ ወደድሁህ ” የተባለ ያዕቆብ
( ሚልክያስ 1 ÷ 2 ሮሜ 9 ÷ 13 )

የእግዚአብሔር ምሕረትና ቸርነት ምን ያህል ታላቅ መሆኑን በኛ መሆንና አለመሆን ላይ በፍፁም የሚደገፍ አለመሆኑን ከማንኛዉም ስዕላዊ መልዕክቶች በበለጠ የምንማረዉ በያዕቆብ ሕይወትና ገጠመኝ ነዉና የገዢዉንና የተወደደዉን ወንድም ያዕቆብን ጉዞ በመከተል ትምህርትን ለመቅሰም እንጥራለንና----- ኑ ! አብረን እንግዋዝ ::

ከሀያ አመት የአጎቱ ቤት ቆይታ በኋላ ፊቱ እንደ ቀድሞዉ ስላልሆነለት ልቡ አዝኖ የሚያደርገዉን ሲያወጣና ሲያወርድ ድንገት እግዚአብሔር ጣልቃ በመግባት ( ዘፍ 31 ÷ 3 ) “ ወደ አባትህ ምድር ወደ ዘመዶችህም ተመለስ ፤ እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ ” የሰጠዉ ተስፋ

“ ሀዉልት የቀባህበት ፤ በዚያም ለእኔ ስዕለት የተሳልህበት የቤቴል አምላክ እኔ ነኝ :: አሁንም ተነስ ! ከዚህ አገር ዉጣ !
ወደ ተወለድህባት ምድር ተመለስ :: ” ( ዘፍ 3 ÷ 13 )
እግዚአብሔር ብሎኛልና ተነሱ እንሂድ እርሱ እንደቃሉ ነዉና ::
ሂዱ ፤ ወጡ ፤ ቀየ ምድራቸዉን ለቀቁ --------ራሄልና ልያ ::

ለተሻለ ኑሮ ፤ የተሻለ ሕይወት ፤ በተሻለ አምላክ ፤ ለመምራት መዉጣት ፤ መሄድ ፤ ግድ ነዉና መለየት :: ትተዉት ሄዱ ላባን ፤ ሳያዉቅ ፤ ሳይጠረጥር ሸሹት ፤ ተለዩት ::

የነፃነት ትንፋሽ ፤ የራስነት ጉዞ ለመልካም ፤ ለጥሩ ሄዱ የእፎይታ እርምጃ ተራመዱ :: መላ ቤተሰቡ

ዘፍ 34 ÷ 1- በከነዓናዉያንና በፌርዛዉያን ምድር እህታቸዉ ተደፈረች :: ዋዉ ! -----ስምኦንና ሌዊ ሄዱ ደምን አፈሰሱ ፤ ለብቀላ እንደገና ፍርሀት ድንጋጤ በቤተሰቡ -----ትንሽዋን ነፃነት ለመንፈግ ፍልምያ ፤ ሰላምን ለመንጠቅ ትግል ::

ምነዉ ? ምነዉ ? በዚህች አገር በሚኖሩ በከነዓናዉያንና በፌርዛዉያን ሰዎች የተጠላሁ ታደርጉኝ ዘንድ እኔን አስጨነቃችሁኝ ? ( ዘፍ 34 ÷ 30 ) እኔ በቁጥር ትንሽ ነኝ :: እነርሱ በእኔ ላይ ይሰበሰቡና ይመቱኛል :: እኔም ከወገኔ ጋር እጠፋለሁ :: ምነዉ ? ምነዉ ?

ጭንቀት ፤ ፍርሀቱን ሳይሸሽግ ለልጆቹ ገለፀ ፤ ያዕቆብ አባታቸዉ :: ዛሬም ፍርሀት ፤ ዛሬም ጭንቀት ፤ አቤት ሕይወት !
በፈራን በደነገጥን ሰዐት ፤ ዙሪያችንን ፍርሀት ሲዉጠን ፤ እርሱ አወን ! እርሱ ብቻ ጉልበት ደገፉ የሚሆን አምላክ ድንገት ይገለፅና መሸሸጊያ ይሆናል

ለያዕቆብም “ ወደ ቤቴል ዉጣ በዚያም ኑር ” ዘፍ 35 ÷ 1
በማለት ድንገት በጭንቀቱ ሰዐት ፤ በድንጋጤዉ ወቅት እግዚአብሔር ደረሰለትና መሸሸጊያ ፤ መጠለያ ሆነዉ :: ለእኔም ለእርስዎም እንዲሁ ነዉ በስሙ ተጠርተናልና ፤ በመንፈሱ ታትመናልና ::
ቤቴል ! የጉብኝት ስፍራ ሳይሆን - የመኖርያ ስፍራ ነዉና በዚያም ኑር !
እርስዎስ በቤቴል እየኖሩ ነዉ ? በእግዚአብሔር መገኘት ዉስጥ ፤ በቃሉ ዙርያ እለት እለት ራስዎን ካላገኙት እ-እ-እ-እ-
ዘፍ 28 ÷ 10-19 ለመጀመሪያ ጊዜ ያዕቆብ ነፍሱን ለማዳን በሮጠ ጊዜ እግዚአብሔር በግልፅ የተገናኘዉ ጊዜ :: ፊት ለፊት አምላኩን ያየበት ስፍራ ፤ ክብሩንና ግርማዉን የተለማመደበት ስፍራ ቤቴል !

ቤቴል ! እግዚአብሔር አልተዉህም ከቶም አለቅህም ብሎ ከስጋ ለባሽ ÷ ያዉም ያዕቆብን ከመሰለ ሰዉ ቃል ኪዳን የተጋባበት ስፍራ ቤቴል:: ወደዚህ ቤቴል ሂድ ፤ በዚያም ኑር :: በሀይለኛ ሰዐት ፤ ረዳት በሻትንበት ወቅት እግዚአብሔር ወደ እኔ መገኘት ዉስጥ ና ÷ ነፍስህ ታርፋለች ፤ ከጥላየ በታች ተሰወር በዚያም ኑር ይላል ::
ያዕቆብ መልሱ አፋጣኝ ነበር ------እሺ-----የሚል እጅን የማንሳት ፤ ካላንተ የለኝም የማለት በአምላኩ የመማረክ ግሩም መታዘዝ :: ያዕቆብ ቤቴል ማንን እንደሚያገኝ ያዉቃልና ዝግጅቱን ቀጠለ ::

1. እንግዶችን አማልክት አስወግዱ
   ከዚህ በፊት ወደ አባትህ ቤት ሂድ ተብሎ የአጎቱን ቤት ሲለቅ ይህንን አላደረገም :: ለምን ?
   ( ራሔል እንኳን ከአባትዋ የሰረቀችዉን አማልክት አስወገደች )
   ቀበሩት ፤ ዳግም ሳያስቡት ፤ ሳያገኙት

2. ንፁህ ሁኑ ( በንስሀ )

3. ልብሳችሁን ለዉጡ ( የአስተሳሰብና የአመለካከት ለዉጥ )

በማለት መወገድ የሚገባዉን ካስወገዱ በኋላ ጉዞ ወደ ቤቴል ወደ እግዚአብሔር ቤት ማንም ሳይደፍራቸዉ ጦር ሳይመዝባቸዉ ተጓዙ ::
የእግዚአብሔር ቤት የአምልኮ ቤት ፤ ስሙን መወደሻ ቤት ያዕቆብ በቤቴል መጀመሪያ ያደረገዉ ይህንኑ ነበር ( ዘፍ 35 ÷ 7 ) ለአምላኩ መስዋዕትን ማቅረብ ነበር ÷ አድርገህልኛልና አመሰግንሀለሁ!

ይህ ነዉ ምኞታችን ፤ ቢሆንልን ፤ እግዚአብሔር ቢረዳን በቤቴል መስዋዕትን ለእግዚአብሔር ማቅረብ ፤ ስሙን መወደስ ታላቅነቱን በዜማ መናገር ፤ ያማረ አምልኮ ለጌታ ------::

ቤቴል ! እግዚአብሔር በዙፋኑ የሚከብርበት ፤ ሁሉን ቻይነቱ የሚነገርበት ፤ ፍቅርና ርህራሄዉ የሚታወስበት ፤ቤቴል የእግዚአብሔር ቤት ፤ ቤቴል የሕዝቡ ፀጋ መቀባበያ ፤ መፈወሻ ቤት ቤቴል---ቤቴል--

ዲቦራ በቤቴል ሞተች የያዕቆብ እናት የርብቃ ሞግዚት ዲቦራ በቤቴል ሞተች :: ያዕቆብ እናቱን ከቤት ከወጣ ጀምሮ አላያትምና ፤ እንደ እናት የሚያያት ዲቦራ በቤቴል ሞተችበት ::

ታላቅ ሀዘን ፤ ታላቅ እንባ ፤ እንባ ፤ እንባ ለዲቦራ የርብቃ ትዝታ ፤ ገፀታ ነችና ምድር አለቀሰ አሎንባኩት ( የእንባ ሽለቆ ) በቤቴል ፤ ዋ ! ዉ ! ለምን ? ለምን ? አሎንባኩት በቤቴል ለምን ? ( ዘፍ 35 ÷ 8 )

" እግዚአብሔር በዚህ ስፍራ አይደለምን ? " ዘፍ 28 ÷ 16 ለምን ? አሎንባኩት በቤቴል :: ለምን ? ለምን ? -----እኮ ለምን ?

ተቆጣ ያዕቆብ ፤ ተበሳጨ ፤ ተናደደና አኮረፈና ባምላኩ ኑ ! ከቤቴል እንዉጣ ( ዘፍ 35 ÷ 16 ) እንሂድ ብሎ ከቤቴል ቤተሰቡን አወጣ ፤ ሄደ ::

ቁጣ ጨካኝ ነዉ ፤ ኀይለኛ :: ቁራጥ ነዉ ደመኛ :: ሄደ የተወደደችዉ ፤ ፍቅረኛዉ ፤ ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ለሰጠላት ለራሔል እንኳን አልተራራላትም እርግዝናዋ አልታየላትም :: የጨከነ ሰዉ ብዙ ፤ ብዙ ያደርጋልና ተነሱ ሄዱ መኖር አልወደዱም ::

አሎንባኩት በቤቴል ያስጨክናል ፤ አምላክ የት አለ ያሰኛል ትርፌ ይህ ነዉን ? ለምን እኔ ? ---በስሙ የተጠራሁ አይደለሁምን ? በበጉ ደም መዋጀቴስ የት አለ ? ምሬት ያመጣል ፤ ያስከትላል !

እርስዎ እንዴት ነዎት ?

ይህን ያህል ቀንዋ ደርሶአልና ራሔል በምጥ ተጨነቀች ፤ ጮኀች ፤ አልቻለችምና ሀዘንተኛ ነችና ስሙን ቤንኦኒ (የሀዘኔ ልጅ) አለችዉ :: ያተረፍኩት ይህንን ነዉ ብላ -----ቤንኦኒ-------

ራሄል ይህንን ብላ ሄደች ፤ አንቀላፋች ወደ ወገኖችዋ ተከማቸች አሎንባኩት-----እንባ ፤ በእንባ ላይም እንባ ፤ ጭንቀት ፤ ለቅሶ ::

ትኩር ብሎ ተመለከተና ፤ አነሳዉ ፤ ያዘዉና የልጅነት ገላዉን ዳሰሰና የለም የለም ! ቢንያም ነዉ ! ቢንያም ! ቢንያም ! ---- ( የደስታየ ልጅ ÷ የቀኝ እጄ ልጅ ) ቢንያም ! ቢንያም ይሁን አለ ያዕቆብ

ከአሁን በኋላ ሀዘን የለም----ለምን ? ለምን ? ሀዘን ተስፋችን በላይ ነዉና በምድር ጊዜአዊና የአሁን ሰዉ ነንና ፤ ደስታየ ይጀምር ቢንያም ብየዋለሁ ፤ ቢንያም ይሁን አወን--ቢንያም--ደስታየ--

ፊሊ 3 ÷ 1 " በቀረዉስ ወንድሞች ሆይ :- በጌታ ደስ ይበላችሁ :: "

ዙሪያችሁ አሎንባኩት ቢሆን :- በጌታ ደስ ይበላችሁ :: ምክንያቱም በእርሱ በመሆናችሁ ብቻ ነዉና ዛሬ ያንቀላፉትን በጌታ ቀን የምታዩአቸዉ ከወዳጆቻችሁ ጋር እንደገና ለዘላለም አንድነት የምትሰበሰቡት ፤ በርቱ !

" በዚች ህይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ ያደረግን ከሆነ ፤ ከሰዉ ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነን :: "

1 ቆሮ 15 ÷ 19

" አወን አሎንባኩት በቤቴልም አለ "

የልጆቹ እንባ የሚታበስበት ጊዜዉ ሩቅ አይደለምና

እ-ን-በ-ረ-ታ-ለ-ን

እ-ና-ደ-ር-ጋ-ለ-ን

እንባዎችንም ሁሉ ከአይኖቻችን ያብሳል ÷
ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም ÷
ኋዘንም ቢሆን ወይም ጩኀት ወይም ስቃይ
ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም
የቀደመዉ ስርት አልፎአልና ::

ራዕይ 21 ÷ 4

# <u>እንዳይደገም</u>

ኢየሱስም :- ሕፃናትን ተዉአቸዉ ወደእኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሉአቸዉ ::

ማቴ 19 ÷ 14

ጌታዉም ባርያዉን :- ቤቴ እንዲሞላ ወደ መንገድና ወደ ቅጥር ዉጣና ይገቡ ዘንድ ግድ በላቸዉ ::

ሉቃስ 14 ÷ 23

እግዚአብሔር ከዘመናት ጀምሮ ለሰዉ ልጆች ያለዉ አላማና እቅድ :- ወደ ራሱ መጥራት ፤ ሕዝቡን መሰብሰብና ማቀፍ ፤ በጥላዉ ስር መሸሸግና መንከባከብ ሲሆን :-

ምነዉ ?

ደቀ መዛሙርቱም ወደ እርሱ ቀርበዉ :------------------ " <u>አሰናብታቸዉ</u> " አሉት ::

ማር 6 ÷ 35-36

ለምን ሕዝብን ከጌታ ለመለየት ቸኮሉ ? ለምን ?
ጠንቀቅ ነዉ ! እንዲ እንዳይደገም ::